# አዚኦን አቡነ ጳውሎስ!!



በደጋጎች ወንበር ያልተቀመጠ!!

**መንገዱ የዋዘኞች፣ የከፎዎቹ መስመር ፣**

**በዋዛ ቆብ ደፍቶ ፣ እንደዚህ ሊሰበር ፣**

**መስቀሉን ለውጦ ፣ ሽጉጥ የተኮሰ፣**

**ሕግህን የተው ፣መነኩሴ ያስለቀሰ ፣**

በቁመናው ሳለ ፣ ሃውልቱን የሰራ ፣

ከንቱ ውዳሴ የሚወድ ፣ ለሰው የማይራራ፣

የሚበላ ጠፍቶ ፣ የሚቀመስ ዳቦ ፣

ሃውልቱን ያቆመ ፣ ሕፃናት አስርቦ ፣

በንጹሕ በፍታ ፣ ስጋው አይከፈን ፣

መቃበሩ ይብላው ፣ የሕዝብ ሁሉ ሃዘን ፣

ይንከባለልበት ፣ ትልቅ ድንጋይ ይጫን::

መቅደስ ያረከሰ ፣ መዓት የወሰደው ፣

ሕግህን የጣላ ፣ዘመኑ እንደሳር ነው !!

**በዐመፃ የተፀነስክ ፣ በኀጥያት የተወለድክ ፣**

**በሕዝቡ የጨከንክ ፣ ዋልድባን የደፈርክ ፣**

**ዐመፃ መንገዱ ፣ በልቡ ሃሳብ ኮርቶ ፣**

**ለታረዘት ሳይሆን ፣ ለበዳይ ሞግቶ ፣**

ሕግጋት ያዛባ ፣ ትእዛዝ ያልጠበቀ ፣

በሚበላ እሳት ፣ ይኸው ተነጠቀ ።

ሁሉ በእርሱ ሆነ ፣ መድሃኒት ሆነልኝ ፣

ሕግ ተላላፊውን ፣ ፈጥኖ ቀሰፈልኝ ፣

ከመንበሩ አዋርደህ ፣ ካፈር ደባለከው ፣

ልቡ የጠመመ ፣ ዘመኑ እንደሳር ነው ።

እግዚአበሔር እግዚእ መስተበቅል።

እግዚአበሔር መስተበቅል ገሃደ።

እግዚአብሔር የበቀል አምላክ ነው።

የበቀል አምላክ ተገለጠ።



መይሳው ከምድረ ስዊድን

2012-08-18